| | |
|---|---|
| ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ<br>ኢየሱስ መሲሕ<br>ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ<br>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ | ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር<br>ድንግል ማርያም<br>እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ<br>ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ |
| የይሁዳው አንበሳ፡ ድል ነሣ!<br>እርሱም፡ በኢትዮጵያዊው መልከ-ጼዴቅ፡ የአጼነት ሹመት ሥርዓት፡<br>የጽዮን ንጉሥ፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች ንጉሥ ኾኖ፡<br>በዘለዓለማዊው ክህነት የሚኖረው፡ ኢየሱስ መሲሕ ነው። | በእግዚአብሔርነቷ፡ እጆቿን ዘርግታ የምትኖረው ኢትዮጵያ፤<br>የአምላክ እናትና የእኛም እናት፤<br>የጽዮን ንግሥት፥ የመላዋ ኢትዮጵያም፡ የንጉሦችና የንግሥቶች<br>ንግሥት፡ እግዚአብሔር እም፥ ድንግል ማርያም ናት። |

---

**ቍጥር ፲፫/፳፻፲ ዓ. ም.**

# ቃለ ዐዋድ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የዐዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

በስመ እግዚአብሔር አብወእም፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሐዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤

በስመ እግዝእትነ ወእምነ፥ ወሀገሪትነ ወሃይማኖትነ፥ ወመድኃኒትነ ወንግሥትነ፡
ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤

በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ ወፈጣሪነ፥ ወአምላክነ ወካህንነ፥ ወሰላምነ ወንጉሥነ ኢየሱስ መሲሕ፡
ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ-ማርያም ሥግው።

ማለትም፡-

በልዩ ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡
በእግዚአብሔር አብወእም፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም፤

እግዚአብሔር እናታችንና አገራችን፥
ሃይማኖታችንና መድኃኒታችን፥ ንግሥታችንም በኾነችው፡
አምላክን በወለደችው፡
በቅድስት ድንግል ማርያም ስም፤

በመለኮትነቱ እና በሰውነቱ፡ የእግዚአብሔር አብ እና የእግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም ልጅ፥
እግዚአብሔር ወልድና ፈጣሪያችን፥ አምላካችንና ካህናችን፥ ንጉሣችንና ሰላማችንም በኾነው፡
በኢየሱስ መሲሕ፡ በመስቀሉ ኃይል።

\+ + +

## ይድረስ፡-

በጌታዬ በፍቅሬ በእግዚአብሔር አብ፥
በልጄ በወዳጄ፡ በእግዚአብሔር ወልድ፥
በሕይወቴ በመድኃኒቴ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፡
የኹለንተና ልጆቼ ለኾናችሁት፥

ስሜ በተጠራባት፡ በኢትዮጵያ ምድር ላላችሁትና
በመላው ዓለም ለተበተናችሁት፥
በልዩ ልዩ ተግባርና ሙያም ለምታገለግሉ፥
በተለያየ የኑሮ ኹኔታና የሥራ መስክ ለምትገኙ፥

ይልቁንም፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከሚለው፡
የመጀመሪያ መታወቂያችሁ ጋር፡
"የኢትዮጵያ ልጆች" የሚለውን የመጨረሻ ስም በመቀዳጀት፡
በቅዱሱ ኪዳን፡ ርስት ጕልቴ ለኾናችሁት፥

በአጠቃላይ፡ እንደኢትዮጵያ ሥርዓተ-መንግሥት፡
የቤተ-ሕዝቡ፥ የቤተ-ክህነቱና የቤተ-ምልክናው አባሎች ለኾናችሁት፡
ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያን እና ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ልጆቼ!

እንዲሁም፡
የሚሰማ መንፈሳዊ ጆሮና የሚያይ መንፈሳዊ ዓይን ላላችሁ፡
በምድር ላይ ለምትኖሩ፡ ለመላው የዓለሙ የሰው ወገኖች ፍጡሮቻችን፥
ለወንዶቹም፡ ለሴቶቹም፥ ለአዛውንቱም፥ ለወጣቶቹም፥
በየግላችሁም፥ ለኹላችሁም!

በአንድ አምላካዊ ፈጣሪነቱ፥ በሥላሴነት መለኮታዊ ቸርነቱም፡ ሙሽራውና እናቱ፥ መቅደሱም ባደረገኝ፡ በልዑል እግዚአብሔር ስም፡ ዘለዓለማዊው፡ የእናትነት ጸጋዬ፡ ፍቅሬና ሰላሜ፥ በረከቴና ረድኤቴ፡ በያላችሁበት ይድረሳችሁ!

እንዳለፈው፡ እንደ፲፪ኛውና ከእርሱ እንደቀደሙት ተከታታይ መለኮታውያት የዐዋጅ ቃሎቼ ኹሉ፡ ዛሬም፡ የምናገራችሁና የማናግራችሁ፡ እግዚአብሔር እናታችሁና ሃይማኖታችሁ፥ አገራችሁና ንግሥታችሁ፥ ክህነታችሁና መቅደሳችሁ፥ እመ-ቤታችሁና ምድረ-ርስታችሁ የኾንሁት፡ እኔው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ድንግል ማርያም ነኝ።**

## መቅድም

በቅዱሱ ኪዳን፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" ከሚለው፡ የመጀመሪያ መታወቂያችሁ ጋር፡ "የኢትዮጵያ ልጆች" የሚለውን፡ የመጨረሻ ስም ተቀዳጅታችሁ፡ ይኸው እንግዴህ፡ ለ፯ሺ፭፻፰ (ሰባት ሽህ አምስት መቶ ስምንት) ዓመታት፡ በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር ሥርዓተ-መንግሥታችን ሥር በሚገኙት፡ በቤተ-ሕዝቡ፥ በቤተ-ክህነቱና በቤተ-ምልክናው የአገልግሎት ዘርፎቻችን ውስጥ አባሎች ኾናችሁ፥ በእውን በሚያየው መንፈሳዊ ዓይን እየተመለከታችሁ፥ በእውን በሚሰማው መንፈሳዊ ጆሮአችሁም እያዳመጣችሁ፡ በያላችሁበት፡ በየሙያችሁ እያገለገላችሁን የምትኖሩት፡ ወንዶቹ ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያን እና ሴቶቹ ኪዳናውያት ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን!

በየግላችሁ ኾነ፥ በኹላችሁም ዘንድ፡ ሰዓትና ኬክሮስ፥ ቀንና ሌሊት፥ መዓልትና ጨለማ፥ ዕለትና ሳምንት፥ ወርና ዓመት፥ ዘመንና ዐውደ-ዘመናት የሌለባችሁ ኾናችሁ፡ ህልውናችሁን፡ በመንፈሳዊቷ የትንሣኤ ሕይወትና በዘለዓለማዊቷ የሰንበት ዓለም፡ በሕያውነት እየቀጠላችሁ ያላችሁ መኾናችሁን አውቃችኋል።

አዎን! እናንተ ልጆቻችን፡ ለዚህ፡ ለመጨረሻው የህልውናና የሕይወት ፍጹምነት ደረጃ፡ እንዲህ፡ የበቃችሁ ስትኾኑ፣ ነገር ግን፡ ለዚህ ታላቅ ጸጋና በረከት ሊበቃ ባልፈለገው፥ ከዚህ የተነሣም፡ ሊበቃ ባልቻለው፡ በተቀረው መናፍስታዊና ሰብኣዊ ፍጥረተ-ዓለም መካከል፡ በምድር ላይና በሕይወተ-ሥጋ የምትመላለሱ በመኾናችሁ፡ በአራተኛው የሥነ-ፍጥረት ቀናችን፡ ባስገኘንላችሁ፡ በፀሓይ፥ በጨረቃና በከዋክብት አማካይነት፡ በሠራንላችሁ የጊዜ መቁጠሪያ ሥርዓት፡ ይኸው፡ የዚሁ ፍጥረተ-ዓለም፡ አካል ከኾነው ኅብረተሰብ ጋር ዐብራችሁ፡ ምድራዊና ሥጋዊ ኑሮአችሁን እንደቀጠላችሁ ትመለከታላችሁ።

ይኹን እንጂ፡ የዚሁ የተቀረው ፍጥረተ-ዓለማችን አካል ኾኖ፡ ከአዳም እና ሔዋን የተገኘው፡ ይኸው ኅብረተሰባዊው ፍጡራችን፡ ፍላጎቱና ምርጫው፡ ያን፡ በዕፀ-ሕይወት አማካይነት፡ በሥጋ ጭምር እንዲወርሳት፡ እኛ፡ አዘጋጅተንለት የነበረውን፡ መንፈሳዊዉን የዘለዓለም ህልውናንና የነጻነት ባለቤትነትን ሳይኾን፥ ነገር ግን፡ በዕፀ-ዕውቀት [በዕፀ-በለስ] አማካይነት፡ ባደረገው፡ በገዛ ክፉ ምርጫው ምክንያት፡ ይኸው፡ ለተወሰነ ዕድሜ፡ በምድር ላይና በሕይወተ-ሥጋ ብቻ ያሳልፉት ዘንድ፡ በላዩ የወደቀችበትን፡ የሞት ህልውና ቀንበር ተሸካሚነትን ኾኖ ቀረ።

እናንተ የኢትዮጵያ ልጆቼ፡ እንዲያ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁና ምግባራችሁ፥ በኢትዮጵያ፡ ሥርዓተ-መንግሥታችን፡ በመልካሙ ሕይወት እየኖራችሁ ሣለ፡ አስቀድሞ፡ ከሦስት ሺህ ዓመታት በፊት፡ ከአሪታውያኑ አይሁድ ካህናት፥ ተከታትሎም፡ ከሺ ስድስት መቶ ዓመታት በፊት፡ ከኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች መነኮሳት፡ በደረሰባችሁ ክፉ ሃይማኖታዊ የቅኝ ተገዢነትና ተፅዕኖ ምክንያት፥ ከዚህ የተነሣም፡ ተፈጥሮአዊው የጊዜ ቀመራችሁ፡ ኹን ተብሎ፡ በእነዚሁ ቅኝ ገዢዎች እንዲቃወስና እንዲዛባ፥ እንዲቀያየርና እንዲመሰቃቀልም በመደረጉ፡ የቀደሙት ምዝላቶቻችሁ ልጆቻችን የሠሩላችሁ፡ እውነተኞቹ የጾሞቻችሁ መግቢያዎቻቸውና ማብቂያዎቻቸው፥ የበዓሎቻችሁም መከበሪያዎቻቸው ትክክለኞች ዕለታት፡ አብዛኞዎቹ፡ ተዛነፉ፤ ተለዋወጡም።

እነዚህ፡ ክፉዎች የሃይማኖት ቅኝ ገዥዎች፡ በዚህ ተጻራሪ ተግባራቸው ብቻ አልተወሰኑም፤ በቅዱሱ ኪዳን የተጠቃለሉትን፥ በእኛና በእናንተ ዘንድ ብቻ፡ ለዝንተ-ዓለም ተጠብቀው የኖሩትን፡ ሰባቱን፡ **መለኮታውያት ቅዱሳት ቃል ኪዳናት** ሳይቀር፡ እነርሱ፡ በሰብአዊ ዘይቤያቸው፡ "ሰባቱ ኪዳናት" ብለው በሰየሚቸው፡ በሌሎች ጸሎቶች ተክተው፡ ሊለውጧቸውና ሊያስወግዷቸው እስከመሞከር ደረሱ እንጂ።

የእኛና የእናንተ የኾኑት፡ ሰባቱ፡ **መለኮታውያት ቅዱሳት ቃል ኪዳናት**፡-

፩. በጋብቻ ምልክትነት የሚካኼደው፡ **"ኪዳነ አዳም ወሔዋን"**፥

፪. በቀስተ-ደመና ምልክትነት የተከሠተው፡ **"ኪዳነ ኖኅ"**፥

፫. በኅብስትና ጽዋ ምልክትነት የተገለጠው፡ **"ኪዳነ መልከ-ጼዴቅ"**፥

፬. በግርዛት ምልክትነት የሚፈጸመው፡ **"ኪዳነ አብርሃም"**፥

፭. በታቦተ-ጽዮን ምልክትነት የታየው፡ **"ኪዳነ ሙሴ"**፥

፮. በዙፋናዊ ዘውድ ምልክትነት የሚታወቀው፡ **"ኪዳነ ዳዊት"**፥

፯. በቅዱስ ቊርባን ምልክትነት፣ ይኸውም፡ በእኔ፡ በእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም እና በልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ትስብእታዊ ሥጋና ደም የታተመው፡ **"ኪዳነ ምሕረት"** የምንላቸው አይደሉምን? አዎን! ናቸው።

ኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች መነኮሳት ግን፡ በእነዚህ፡ ቅዱሳት ኪዳናት ላይ የፈጸሙትን ደባ፡ እስኪ ስሙት! ዕወቁትም! ከየድርሳናቱ አውጣጥተውና አቀነባብረው፥ አዘጋጅተውም፥ በእነዚህ፡ በእኛዎቹ ቦታ የተኳቸው፥ እነርሱ፡ "ሰባቱ ኪዳናት" ያሏቸው ጸሎቶች፡ እነማን እንደኾኑ ታውቋቸው ዘንድ፡ እነርሱው በሰጧቸው የስም አርእስታቸው፡ እኒኸውላችሁና፡ ስሟቸው!

፩. "ትምህርተ ኅቡዓት"፣ ፪. "ጸሎተ-ኪዳን"፣ ፫. "እግዚአብሔር፡ ዘብርሃናት"፣ ፬. "በእንተ ቅድሳት"፣ ፭. "ቅዳሴ እግዚእ"፣ ፮. "ፍትሐት ዘወልድ" እና ፯. "ሰአልናከ" የሚባሉት ናቸው።

እንግዴህ፡ ከዚህ የጥፋት ድርጊታቸው ጋር፡ ተመሳሳይ በኾነው፣ ቀደም ብዬ ባወሳሁት፡ በአጽዋማቱ እና በበዓላቱ ቀመር ላይ የፈጸሙት፡ የተሳሳተው ሓሳዊ አሠራራቸው፡ በማኅበርና በይፋ ሲካኼድ የኖረው፡ ምንም እንኳ፡ በየውስጥ ሰውነታችሁ፡ ትክክለኛውንና እውነተኛውን ሥርዓት ተከትላችሁ፡ ስትፈጽሙት በቀጠላችሁት፡ በእናንተ፡ በልጆቻችን ዘንድ ሳይኾን፡ በእነዚያዎቹ፡ የተፃራሪዎቻችሁ ደጋፊዎች በኾኑ ወገኖቻችሁ ዘንድ መኾኑን፡ እኛ፡ በእግዚአብሔርነታችን እናውቀዋለን።

ይኹን እንጂ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በእኔ በእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም እና በልጇ በወዳጇ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ፡ እንዲህ በተገለጠችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ዘንድ፡ ይህ የተሳሳተው ሓሳዊ አሠራር፡ ከዚህ በኋላ፡ በዚህ መልኩና ይዘቱ ሊቀጥል እንደማይችል፡ ኹሉም፡ ሊያውቀውና ሊገነዘበው ይገባል።

ስለዚህ፡ ከመጀመሪያዎቹ ፍጡሮቻችንና ልጆቻችን፡ ከአዳም እና ሔዋን አንሥተው፡ በምድር ላይ የነበሩት የቀደሙት ምዝላቶቻችሁ፡ በየዐውደ ዓመቱ፡ ያለማቋረጥ ሲጾሟቸውና ሲያከብሩዋቸው የኖሩት አጽዋማትና በዓላት፡ የትኞቹ መኾናቸውን፥ የሚውሉባቸውም ጊዜያት መቼ እንደኾኑ፡ ለይታችሁ ታውቋቸው ዘንድ፡ ይህን፡ እግዚአብሔራዊ እውነታ፡ በዚህ፡ በእኔው የዐዋጅ ቃል፡ ራሴ እንዳሰማችሁ ፈቀድሁ።

## የዓመቱ አጽዋማትና በዓላት።

የዓመቱን አጽዋማትና በዓላት በሚመለከት፡ በተለይ፡ የእኛ፡ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ሕያው ቅርስ ኾኖ የኖረውን ሥርዓት፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ልጆቻችንና ነጋሢዎቻችን፥ ካህናት አገልጋዮቻችንም ለኾናችሁት፡ ለእናንተ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ከዚህ በሚከተለው የዐዋጅ ቃሌ አሰማችኋለሁና፡ ሰምታችሁ የምትፈጽሙት ይኹን!

በቅድሚያ፡ የእኔ፡ የእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም እና የልጇ የወዳጇ፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ የኾኑትን፡ እነዚህኑ፡ የዓመቱን አጽዋማትና በዓላት፡ የእኛ ልጆቻችን፥ የእናንተም፡ የቀደሙት ምዝላቶቻችሁ የኾኑት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በእየራሳቸው አሳቢነትና ወጣኝነት፥ ፍላጎትና ፈቃድ፡ በእውነትና በመንፈስ አምልኳቸው አማካይነት፡ ለዝንተ-ዓለም፡ ሲጾሟቸውና ሲያከብሯቸው እንደኖሩ ታውቃላችሁ፤

ቀጥሎ፡ እንደእነርሱ ኹሉ፡ እናንተም፡ የዛሬዎቹ ልጆቻችን፡ እስካኹን፡ በውስጣችሁና በየግላችሁ፡ እንዴት ስትጾሟቸውና ስታከብሯቸው እንደኖራችሁ፡ በእየራሳችሁ ትገነዘቡታላችሁ፤

በመጨረሻ፡ እነዚሁ አጽዋማትና በዓላት፡ በዓመቱ ዑደታቸው ጊዜ፡ እንዲውሉባቸው የተደረጉትን ዕለታት፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁ አቋም ለመቀበል፡ የቱን ያህል ያዳግታችሁ እንደነበረ ታዘክሩታላችሁ።

ከዚህ የተነሣ፡ እናንተም፡ እንግዲህ ወዲህ፡ እነዚህኑ አጽዋማትና በዓላት፡ በዓመቱ ዑደታቸው ውስጥ፡ ይጾሙባቸውና ይከበሩባቸው በነበሩት፥ በእነዚያዎቹ፡ በትክክለኞቹና በመደበኞቹ ቀኖቻቸው፡ ከዚህ በሚከተለው ሥርዓት መሠረት፡ መጾማችሁንና ማክበራችሁን ትቀጥሉ ዘንድ፡ ይህን ማሳሰቢያ፡ በእኔው የዐዋጅ ቃል፡ እንድትሰሙት፡ አስፈላጊ ኾነ።

ይኸውም፡ በአኹኑ ጊዜ፡ ራሷን፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ ገልጣ፡ ቸርነቷን በይፋ ማካኼድና መፈጸም በጀመረችው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ዘንድ፡ ያንኑ፡ የኪዳናውያኑንና የኪዳናውያቱን ምዝላቶቻችሁን ፈለግ ተከትላችሁ የምታደርጉት፡ ያው ሥርዓት መኾኑ ሊታወቅ ይገባል።

በዚህ ሥርዓት መሠረት፡ ከኹሉ አስቀድሞ፡ ከዓመታቱ ዕለታት መካከል፡ በየሳምንቱ እየተከታተሉና እየተዘዋወሩ የሚመጡት፡ በተለይም፡ **የመጋቢት ፳፱ኛ ዓርብ**፥ **የመጋቢት ፴ዋ ሰንበትና የሚያዝያ ፩ዱ እሑድ**፡ በመታሰቢያነት የሚከበሩ ቀዳሚዎቹ፡ የሳምንት በዓላት ይኾናሉ። የእነርሱንም ዝርዝር ምንነት፡ እንዲህ በሚለው አጫጭር ማብራሪያዬ ተረዱት!

ዓርብ፡-

-እኔ፡ እግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ገና ጥንቱኑ፡ የክፋት ተገዦች ሊኾኑ ለተዘጋጁት አዳም እና ሔዋን፡ ሕይወትና ዕውቀት ልኾናቸው፡ በገነት፡ በዕፀ-ሕይወትነትና በዕፀ-ዕውቀትነት የበቀልሁባት፥

-ከዚያም፡ በክፋት ለበደለው ለሰብአዊው ፍጥረተ-ዓለም ቤዛ ኾኜ ልታደገው፡ በመጀመሪያ በኖኅ መርከብነት የተገለጽሁባት፥

-ኋላም፡ በጣዖት-አምልኮ የኃጢአት ቀንበር ተወድሮ የሚማቅቀውን ሰብአዊ ፍጡራችንን፤ ደግሞም፡ ከቃል ኪዳን አፍራሽነታቸው የተነሣ ሊደመሰሱ፡ መለኮታዊው ሠይፍ የተመዘዘባቸውን፡ የእስራኤልን ልጆች ጭምር፡ በመድኃኒትነቴ ለማትረፍ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ እኔ እግዚአብሔር እም፡ አስቀድሜ፡ ኹለቱን የደብረ-ሲና፡ ዕብነ-በረድ ሰሌዳዎች የተዋሓድሁባትና የልጄን የወዳጄን የእግዚአብሔርን ቃልነት፡ በእግዚአብሔር አብ ጸሓፊነት፡ እንዲቀረጽብኝ በማድረግ፡ "ጽላተ-ሙሴ" የተባልሁባት፥

-በመጨረሻም፡ ለክፋቱ አበጋዝ ለዲያብሎስ፡ ያለውን ተገዢነቱን ለቀጠለው፡ ለመላው የሰው ዘርና ፈጽመው ለጠፉት ለእስራኤል ልጆች መዳን፡ ምክንያት እኾን ዘንድ፡ እኔ እግዚአብሔር እም፡ አኹንም እንደገና፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ድንግል ማርያምን አስቀድሜ ተዋሕጄ፡ ባስገኘሁት <u>መድኃኒትነቴ</u>፡ ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእኔ በተወለደበት ሰውነቱ፡ የሓሰቱንና የክፋቱን የጠላትነት ጦር፡ በእውነትና በፍቅር ጋሻ፡ መጀመሪያ፡ ከፍጥረት ልደት አንሥቶ፡ በመለኮትነት ልጅነቱ፥ ኋላም፡ በፍጻሜ ዘመን፡ በትስብእት ልጅነቱ፡ ባደረገው የመከላከል ተጋድሎው፡ ለማብቂያው የድል አክሊል ያደረሰውን መሥዋዕትነቱንና ቤዛነቱን በፈጸመባት፡ በዚያች፡ ጥንተ ስቅለቱና የመስቀል ሞቱ ዕለት በኾነችው፡ በመጋቢት ፳፱ ቀን፡ የዘለዓለም <u>ሰላምን፡</u> ለፍጥረተ-ዓለሙ አረጋግጦና አስተማምኖ ያጐናጸፈባት ስለኾነች ነው።

እዚህ ላይ፡ እናንተ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ፡ <u>"ብኪ ድኅነ ዓለም! ወበወልድኪ ኮነ ሰላም!</u>

<u>"ፍጥረተ-ዓለሙ ኹሉ፡ በአንቺ ዳነ! በልጅሽም፡ ሰላም ኾነ!"</u> እያላችሁ፡ በምስጋና ጸሎታችሁ የምታሰሙት መዝሙራችሁ፡ እውን የኾነባት ዕለት መኾኗ እንደታወቀ አስተውሉ።

<u>ሰንበት፡-</u>

-በቀዳማዊው የፍጥረት ዘመን፡ "ወባረካ እግዚአብሔር፡ ለዕለት ሳብዕት፤ ወቀደሳ፤ እስመ ባቲ አዕረፈ እምኵሉ ግብሩ፡ ዘአኀዘ ይግበር።

"እግዚአብሔርም፡ ሰባተኛዋን ቀን ባረካት፤ ቀደሳትም፤ የጀመረውን የመፍጠር ሥራውን ኹሉ ፈጽሞ፡ በእርሷ ዐርፎባታልና።" የተባለችው ናት፤

-በመካከለኛውም የሕግ ዘመን፡ "ተዘከር፡ ዕለተ ሰንበት፡ ከመ ትቀድሳ! ሰዱሰ ዕለተ ትገብር ኵሎ ግብረከ፥ ወኵሎ ትካዘከ! ወሳብዕት ዕለት፡ ሰንበቱ፡ ለእግዚአብሔር አምላክከ፤ ኢትግበር ባቲ፤ ወኢምንተኒ ግብረ!

"የሰንበትን ቀን ትቀድሳት ዘንድ፡ አስብ! በስድስቱ ቀኖች፡ ሥራህን ኹሉ፥ ግዳጅህንም ኹሉ አድርግ! ሰባተኛዋ ቀን ግን፡ የአምላክህ የእግዚአብሔር ሰንበቱ ናትና፡ በእርሷ፡ አትሥራ! ምንም ዓይነት ተግባርን አታድርግ!" የተባለላት፡ እርሷው ናት፤

-በፍጻሜውም የሕይወት ዘመን፡ ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ "ይከውንኑ በሰንበት፡ ገቢረ ሠናይ? ወሚመ፡ ገቢረ እኩይ? አሕይዎ ነፍስኑ? ወሚመ፡ ቀቲል?

"በሰንበት፡ ማድረግ የሚገባው፡ በጎ ነገርን ነውን? ወይስ፡ ክፉ ነገርን? ነፍስ ማዳን? ወይስ፡ መግደል?" ብሎ፡ ላቀረበላቸው ጥያቄ፡ መልስ ስላልሰጡት፡ ለተቃዋሚዎቹ አይሁድ፡ ሕሙማንን በመፈወስ፡ በሰንበት፡ በጎ ማድረግና ማዳን እንደሚገባ፥

ደግሞም፡ "ሰንበትሰ፡ በእንተ ሰብእ ተፈጥረት፤ ወአኮ ሰብእ፡ በእንተ ሰንበት። ወወልደ እጓለ እመሕያው ውእቱ፡ እግዚኣሃ፡ ለሰንበት።

"ሰንበትማ፡ ስለሰው ተፈጠረች እንጂ፡ ሰው፡ ስለሰንበት አልተፈጠረም። የማርያም ልጅ፡ የሰንበት፡ ጌታዋ ነው።" ብሎ በማብራራት፡ የተናገረላት ናት።

"በአጠቃላይ፡ ልጁ ወዳጁ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመስቀል ላይ ኾኖ፡ "ተፈጸመ ኵሉ! እንግዴህ፡ ኹሉ ተፈጸመ!" ብሎ፡ ዓርብ፡ በመጋቢት ፳፱ ቀን፡ ነፍሱን፡ በሥልጣኑ፡ ከሥጋው ከለየ በኋላ፡ "ወአይሁድሰ፡ እስመ ዐርብ ውእቱ፡ ይቤሉ፡ 'እላንቱ ሥጋት፡ ኢይቢታ ዲበ መሳቅሊሆን፡ በእንተ ሰንበት፤ እስመ ዐባይ ዕለታ፡ ለይእቲ ሰንበት!'

"አይሁድ ግን፡ መሸቷልና፡ 'እነዚህ አስከሬኖች፡ ስለሰንበት፡ በየተሰቀሉበት አይደሩ! የዚች ሰንበት ቀን፡ ታላቅ ናትና!' አሉ።" የተባለችው፡ ይህችው፡ አንዷቷ ሰንበት ናት።

እንግዴህ፡ ያች፡ "እግዚኣሃ፡ ለሰንበት!" "የሰንበት፡ ፈጣሪዋና ጌታዋ የኾነው፡ ልጁ ወዳጁ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በሰውነቱ ሞቶ ሣለ፡ መለኮትን የተዋሓደ ሥጋውን፡ በመቃብር አሳድሮ ያረፈባት፥ ነጻነትንም ለማወጅ፡ በነፍሱ፡ ወደሲዖል ወርዶ ያሳለፋት፡ የመጋቢት ፴ዋ ቀን፡ የሰሙነ ሕማማቷ ሰንበት፡ ይህችው አንዷቷ ሰንበት ናት። "(ዘፍጥ. ፪፥ ፫። ዘፀአ. ፳፥ ፰-፲፩። ማር. ፪፥ ፳፯-፳፰፤ ፫፥ ፫-፬። ዮሐ. ፲፱፥ ፴፩።)

ሌላ ኹለተኛ ሰንበት ያለች ይመስል፡ ይህችው፡ አንዷቷ ሰንበት፡ "ቀዳሚት" ወይም፡ "ቅዳሜ" የሚል መለያ ስም ተሰጥቷት መኖሯ፥ ደግሞም፡ "ሰንበተ አይሁድ"፡ "የአይሁድ ሰንበት" እየተባለች መጠራቷ፥ ይልቁንም፡ "ቅዳሜ ስዑር"፥ ወይም፡ "ከሰንበትነቷ የተሻረች ቅዳሜ" ስትባል መኖሯ፡ አግባብ እንዳልኾነ፡ በሚያዝያ ፩ ቀን በኾነው፡ በልጁ ወዳጁ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ትንሣኤ የተከሠተችው፡ የእግዚአብሔር እውነት አረጋግጣ አመልክታለች።

የሰንበት ጌታ እርሱ፡ ልጁ ወዳጁ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ዓርብ፡ በመጋቢት ፳፱ ቀን፡ በሥጋው ሞቶ፡ በመጋቢት ፴ ቀን የመቃብር ዕረፍቱን፡ ያሳለፈባት ስለኾነች፡ ዕለቷ፡ ከሰንበትነቷ እንደተሻረች በመቍጠር፡ ይህ፡ ልዩ ስያሜ ተሰጥቷት መቆየቱ፡ ፍጹም ስሕተት መኾኑ፡ "በእውነትና በመንፈስ" አምልኮ ጸንታ በምትኖረው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ዘንድ እሙን ነው።

"ቅዳሜ ስዑር" በተባለችው፡ በዚችው ዕለት፡ የኾነውን መለኮታዊ ድርጊት፡ በእውነት አስተውለው ሲመለከቱት፡ ልጁ ወዳጁ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመጋቢት ፴ ቀን፡ በመቃብር ውስጥ፡ በሥጋው ያረፈባት በመኾኗ፡ በአንድ በኩል፡ "ተዘከር፡ ዕለተ ሰንበት፡ ከመ ትቀድሳ!"

"የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ!" በምትለው፡ በዐሥሩ የኦሪት ቃላት መሠረት፡ ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ዕለቲቱን፡ በሰንበትነቷ አከበራት እንጂ፡ አልሻራትም፤ በሌላው በኩል ደግሞ፡ በትንሣኤው፡ **ይህችኑ አንዲቷን ሰንበት፡ ሕያውትና ዘለዓለማዊት ኾና እንድትቀጥል አድርጓታል።**

**እሑድ፡**

የጥንተ ኦኗ [የፀሓይዋ=የሰብኣዊቷ] ሰንበት፡ በሚያዝያ ፩ ቀን በኾነው፡ በኢየሱስ መሲሕ ትንሣኤ፡ ወደቀደመው እግዚአብሔራዊና ጥንተ-ተፈጥሮአዊው ሰንበትነቷ ተመልሳ፡ ዘለዓለማዊ ህልውናዋን፡ እንዲህ የቀጠለች መኾኗን ያረጋገጠችባት ዕለት ናት።

በዚህ መሠረት፡ ይህችው፡ አንዲቷ ሰንበት፡ በአንድነቷ ጸንታ፡ በሕያውነትና በዘለዓለማዊነት ቀጠለች እንጂ፡ "ሰንበተ ክርስቲያን" የተባለች፡ ሌላ ኹለተኛ ሰንበትን አላስገኘችም። ጥንቱንም፡ ይህችኑ፡ አንዲቷን ሰንበት የፈጠረውና ኋላም፡ "እግዚኣሃ ለሰንበት"፡ "የሰንበት ጌታዋ" የተባለው፡ ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ይህችኑ፡ አንዲቷን ሰንበቱን፡ በትንሣኤው፡ ሕያውትና ዘለዓለማዊት አደረጋት እንጂ፡ ሌላ፡ ኹለተኛ ሰንበትን አልፈጠረም፤ አልሠራም። ይህ፡ ኹለት ሰንበታት እንዳሉ የሚያስመስለው ትምህርትና ሥርዓት፡ የሰዎች እንጂ፡ የእግዚአብሔር አለመኾኑ፡ በዚህ እውነታ፡ ተረጋግጦ ይታወቃል።

እኛ እግዚአብሔር፡ በፈጣሪነታችን በሠራነው፡ በሥጋዊው የፍጥረት ባሕርይና የተፈጥሮ ሥርዓታችን፡ በአንዲት ሰብኣዊት ቀን ተወስና፥ በስሑታን ሰዎች ሥርዓትና ይትበሃል ግን፡ አላገባብ፡ "ቅዳሜ"፥ "ቀዳሚት ሰንበት"፥ "ሰንበተ አይሁድ" እና "ቅዳሜ ስዑር" እየተባለች ስትዘከር ቆይታ፡ በመጨረሻ፡ የዘመነ ኵነኔ ማብቂያና የዘመነ-ምሕረት መባቻ በኾነችው፡ ልክ፡ በዚችው ዕለተ ሰንበት፡ ደኃራይ ሰዓተ [መንፈቀ] ሌሊትና በእሑድ ቀዳማይ ሰዓተ [ነግሀ] መዓልት ቅጽበት ላይ፡ **በሚያዝያ ፩ ቀን ተፈጽሞ በተከሠተው፡ በልጇ በወዳጇ በኢየሱስ መሲሕ ትንግርታዊ ትንሣኤ፡** የጊዜ ጽንፍ ለሌላት፡ ለቀደመችይቱ፡ የእኛዋ ሰንበትነቷ የበቃችው፡ ይህችው፡ አንዲቷ ሰንበት ናት።

በዕለተ-እሑድ፡ "ሰንበተ ክርስቲያን" የተባለችው፡ ሌላ፥ ወይም፡ ኹለተኛ ሰንበት አይደለችም፤ ይህችው፡ በዘልማድ፡ "ቅዳሜ"፥ "ቀዳሚት ሰንበት"፥ "ሰንበተ አይሁድ"፥ "ቅዳሜ ስዑር" እየተባለች የኖረችው፥ ከፍጥረት ልደት ጀምሮ፡ "ሰንበተ ኢትዮጵያ" ኾና፡ በህልውናዋ የቀጠለችው፡ አንዲቷ ሰንበት ናት እንጂ።

ከዚህ የተነሣ፡ ከመጨረሻው፡ የትንሣኤ ዘጉባኤ በፊት፡ **"ብፁዕ ወቅዱስ ውእቱ፡ ዘረከበ ክፍለ፡ በትንሣኤ እንተ ትቀድም መጺአ!**

"አስቀድማ በምትመጣው ትንሣኤ፡ ዕድል ፈንታ ያገኘ ሰው፡ ብፁዕና ቅዱስ ነው!" ተብሎ እንደተነገረው፡ ዛሬም እንኳ፡ በዚሁ፡ በልጇ በወዳጇ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ትንሣኤ በተገኘው፡ በመጀመሪያው፡ የሺሁ ዓመት የመንፈስ የትንሣኤ ሕይወት ለመኖር የበቁት፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ጭምር፡ ወሰን በሌላት፥ ሕያውትና ዘለዓለማዊት በኾነችው፡ በዚችው፡ በአንዲቷ ሰንበት፡ እነሆ ይኖራሉ። (ራእ. ፳፥ ፮።)

እነዚህ፡ ሦስቱ፡ ሰሙናዊ [የሳምንት] ዕለታት፡ በጾምነትና በበዓልነት የሚፈጸሙበትና የሚከበሩበት መልክና ይዘት፡ እንዲህ የተጠበቀ ኾኖ፡ እውነተኞቹ የዓመቱ ጾሞቻችሁና በዓሎቻችሁ፡ ከዚህ የሚከተሉት መኾናቸውን ዐውቃችሁ፡ እነርሱን፡ ከዚህ ጋር፡ አያይዤ በምገልጽላችሁ መንፈስና ሥርዓት መሠረት፡ በትክክል እንድትጸሟቸውና እንድታከብሩዋቸው ይኹን!

፩ኛ. <u>መስከረም ፩ ቀን</u> የሚውሉትን፡-

-አዳምንና ሔዋንን ያስገኘው ፍጥረተ-ዓለም የተገለጠበትን፤

-ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለግዙፉ ፍጥረተ-ዓለም የተከሠተችበትን፤

-እኔ እግዚአብሔር እም፡ ድንግል ማርያም በትስብእትነት፡ ከቅዱስ ኢያቄምና ከቅድስት ሐና የተወለድሁበትን፤

-ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከእኔ፡ በሰውነት የተወለደበትን መታሰቢያ በዓሎቻችንን ታከብራላችሁ።

፪ኛ፡ <u>መስከረም ፰ ቀን፡</u> የልጇ የወዳጇን የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን የግዝረት ሥርዓት-ኦሪት መታሰቢያ በዓል ታከብራላችሁ። ይህ፡ የእርሱ ግዝረት፡ መለኮታዊና ትስብእታዊ ኾኖ፡ በእግዚአብሔር እውነትና በመንፈስ እንጂ፡ እንደኦሪቱ ሥርዓት፡ በሰውኛ ልማድና በሥጋ የተፈጸመ አይደለም። ይህም ማለት፡ እንደኅጽውነቱ [እንደጃንደረባነቱ]፡ በተፈጥሮው ተገርዞ እንጂ፡ የሚገረዝ ሸለፈት [ትርፍ] ሥጋ ያለው ኾኖ የተወለደ እንዳይደለ፥ ደሙም፡ በመስቀል ጅራፍና የሾህ አክሊል፥ ጦርና ችንካር እንጂ፡ በግዝረት ስለት ሊፈስስ የተዘጋጀ እንዳልነበረ፡ ልታውቁት ያስፈልጋችኋል።

፫ኛ፡ <u>መስከረም ፳፩ ቀን፡</u> ነሓሴ ፲፮ ቀን ከኾነው፡ ከፍልሰት ትንሣኤዬ፡ አርባ ዕለታት በኋላ የደረሰውን፡ የፍልሰት ዕርገቴን መታሰቢያ በዓል ታከብራላችሁ።

፬ኛ፡ <u>መስከረም ፳፮ ቀን፡</u> በሕይወት ዛፍነቴ ያስገኘሁትን መለኮታዊዉንና ትስብእታዊዉን ፍሬ፡ ልጄን ወዳጄን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን ከመጽነሴ በፊት፡ በሴትነቴ ታይቶኝ፡ እናትነቴን ያረጋገጥሁበትን፥ በደስታም የፈካሁበትን፡ ቅዱሱን የወር አበባዬን ምሥራች በማዘከር፡ እናንት የቅዱሱ ኪዳን ልጆቼ፡ ሐሤታችሁን፡ በዓለ-ቊስቋም እስከሚውልበት፡ እስከኅዳር ፮ ቀን ድረስ፡ የዘለዓለማዊቷ ሰንበት መታሰቢያ በኾነችው፡ በየሳምንቷ ዕለተ-እሑድ፡ በዝማሬና በሽብሸባ የምትገልጹበት፡ **የጽጌ ማኅሌታችሁ መግቢያ ነው።**

፭ኛ፡ <u>ጥቅምት ፲ ቀን፡</u> የልጄ የወዳጄን የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን በአተ-መቅደስ [በተወለደ በአርባ ቀኑ፡ ከእግዚአብሔር ፊት የመቅረቡን ሥርዓተ-ኦሪት] መታሰቢያ በዓል ታከብራላችሁ።

እነዚህን የመታሰቢያ በዓላት፡ እስከዚህ ቀን ድረስ፡ ለአርባ ዕለታት የምታከብሩዋቸው፡ ያለጾም፡ በፋሲካ የሐሤት ሥርዓት ይኾናል።

፮ኛ፡ <u>ጥቅምት ፲፩ ቀን፡</u> ከፍጡሮቻችን ከሰዎች፡ ከወንዶችም፥ ከሴቶችም ኹሉ፡ ስደትን፡ ለዘለዓለም ለማስወገድ ስንል፡ በባለሟላችን ሊቀ መላእክት ዑራኤል መሪነትና በታማኞቻችን በዮሴፍና በሰሎሜ አገልጋይነት፡ እኔና ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ሕፃን ኢየሱስ መሲሕ፡ ወደኢትዮጵያና ግብፅ ያደረግነው፥ **ማብቂያውም፡ ኅዳር ፭ ቀን የኾነው፡** "**ጾመ-ስደት**" ብላችሁ የምትጾሙት፡ የስደታችን ዝክር [መታሰቢያ] **ጾም መግቢያ ነው።**

፯ኛ፡ <u>ኅዳር ፮ ቀን፡</u> ለ፳፭ ዕለታት ከጾማችሁ በኋላ፡ የነፍስ፥ የሥጋና የመንፈስ ስደትን፡ ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፡ ከሰው ኹሉ ያስወገድንበትን ድል በማዘከር፡ "**በዓለ-ቊስቋም**" ብላችሁ፡ መታሰቢያ በዓሉን ታከብራላችሁ።

፰ኛ፡ <u>ኅዳር ፲፮ ቀን፡</u> የልጄ የወዳጄን የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን በሰውነት ተወልዶ፡ በዚህ ዓለም የመገለጡን ትንቢትና ተስፋ፡ በጽኑ የጉጉትና የናፍቆት ጾም ተጠምደውና ተመስጠው፡ ይጠባበቁ የነበሩት ነቢያት፡ የነበሩበትን የሱባኤ ትጋህ በማዘከር፡ የትንቢታቸውና የተስፋቸው ፍጻሜ የኾነውን፡ እርሱን፡ ልጄ ወዳጄን እግዚአብሔር ወልድ ሕፃን ኢየሱስ መሲሕን ከመጽነሴ በፊት፡ ለ፲፭ ዕለታት የምትጾሙትና በኅዳር ፴ ቀን የሚያበቃው፡ **የነቢያት ጾም መግቢያ ነው።**

፱ኛ፡ <u>ኅዳር ፳፩ ቀን፡</u> እኔ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም፡ በመስከረም ፩ ቀን፡ በሰውነት ተወልጄ፡ ሰማንያ ቀን ሲሞላኝ፡ እንደኦሪቱ ሥርዓት፡ በቤተ-መቅደስ፡ በእግዚአብሔር ፊት የቀረብሁበት ዕለት ሲኾን፥ ከዚህ ጋር ደግሞ፣

በመጀመሪያ፡- የእስራኤልን ልጆች፡ በታማኙ አገልጋያችን፡ በሙሴ መሪነት፡ ከግብፅ የባርነት ተገዢነታቸው ነጻ አውጥተን፡ ከሲና ምድረ በዳ አንሥቶ፡ ምድረ-ከነዓን እስከገቡበት ጊዜ ድረስ፡ በአርባው ዓመታት የመከራ ጉዟቸው፣

ከዚያ በኋላም፡ በዚያ እየኖሩ ሣሉ፡ የክህደትና የዓመፅ፣ የአምልኮ አመንዝራነትና የክፋት ኃጢአታቸው ጽዋ በመሙላቱ፡ በናቡከደነጾር ጦር፡ የቅጣት ዕልቂት ደርሶባቸው፡ የተረፉት፡ እንደገና ወደባቢሎን ምርኮ ከመወሰዳቸው በፊት፡ ታማኟ ተጠሪያችን በኾነችው፡ በኢትዮጵያዊቷ ልጃችን፡ በንግሥት ማክዳና በልጇ በዕብነ-መለክ አማካይነት፡ ርስት-ጒልቴ ወደኾነችው፡ ወደምድረ-ኢትዮጵያና የቃል ኪዳን ሕዝቤ ወደኾኑት፡ ኢትዮጵያውያትና ኢትዮጵያውያን ልጆቼ እስክመለስ ድረስ፡ በታቦተ-ጽዮንነቴ፡ ስጠብቃቸው የኖርሁበት፡ ረዥም ዘመን የሚዘከርበት ዕለት ስለኾነ፡ በመታሰቢያነት ታከብሩታላችሁ።

፲ኛ፡ <u>*ታኅሣሥ ፩ ቀን፡*</u> በባለሟላችን በሊቀ-መላእክት ገብርኤል ቃለ-ብሥራት [የምሥራች ቃል]፡ ልጄ ወዳጄን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን የፀነስሁበት በመኾኑ፡ ይህንኑ በማዘከር፡ ዕለቱን፡ "በዓለ-ትስብእት" ብላችሁ፡ በመታሰቢያነትታከብሩታላችሁ።

፲፩ኛ፡ <u>*ታኅሣሥ ፫ ቀን፡*</u> ወላጆቼ፡ ኢያቄም እና ሐና፡ እኔን እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያምን፡ በሦስት ዓመት፡ ከሦስት ወሬና ከሦስት ቀኔ፡ ወደቤተ-መቅደስ ወስደው፥ በዚያም አስገብተው፥ በዚያ፡ ልጄ ወዳጄን፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ ቀድሞ፡ በመለኮትነቱ፡ ፀንሼ እንደወለድሁት ኹሉ፡ አኹን ደግሞ፡ በትስብእትነቱ፡ ፀንሼ እስክወልደው ድረስ፡ በዚያ ቤተ-መቅደስ፡ በመለኮታዊትና በትስብእታዊት ታቦተ-ጽዮንነቴ፥ በመድኃኒትነቴም፡ በሕያው ሰውነቴ የምቆይበት በመኾኑ፡ "በዓለ-በአታ-ለማርያም" ብላችሁ በማዘከር፡ ዕለቲቱን፡ በመታሰቢያነት ታከብሩዋታላችሁ።

፲፪ኛ፡ <u>*ታኅሣሥ ፯ ቀን፡*</u> እኔ ድንግል ማርያም፡ ከአዳማዊው ወላጄ፡ ከኢያቄም አብራክ ወጥቼ፡ በሔዋናዊቷ ወላጄ፡ በሐና ማሕፀን በተፀነስሁ ጊዜ፡ እኔ እግዚአብሔር እም፡ በዚችው ዕለት፡ በመለኮታዊትና በትስብእታዊት ታቦተ-ጽዮንነቴ፥ በመድኃኒትነቴም፡ እኔን ድንግል ማርያምን፡ የተዋሓድሁባት ስለኾነች፡ ይህችን ዕለት፡ "በዓለ-ፅንሰታ ለድንግል ማርያም" ብላችሁ በማዘከር፡ በመታሰቢያነት በዓል ታከብሩዋታላችሁ።

፲፫ኛ፡ **ጥር ፩ ቀን፡** የልጇ የወዳጇን የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ በዓለ አስተርእዮቱንና ጥምቀቱን፡ በመታሰቢያነት ታከብራላችሁ።

የምታከብሩትም፡ እንደተለመደው፡ እናንተ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ፡ በየዓመቱ፡ በታኅሣሥ ፴ ቀን በሚውለው፡ የጥምቀት ዋዜማ፡ ለማጥመቅ ሥርዓታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ውኃ፡ ከወንዝ ጠልፋችሁ የምትከትሩበት፡ ቀን በመኾኑ፡ "ከተራ" ብላችሁ፥ ደግሞም፡ ቅዱስ ቍርባንን የምትቀበሉበት በዓላችሁ ስለኾነ፡ የአንዲት ቀን ጾማችሁን፡ "ገሀድ" ብላችሁ በምትጠሩት፡ የእውነትና የመንፈስ አምልኮ ዝግጅታችሁ ይኾናል።

የጥምቀት ዋዜማው ከተራና የገሀድ ጾሙ፡ በታኅሣሥ ፴ ቀን፥ በዓለ አስተርእዮቱና ጥምቀቱ ደግሞ፡ በጥር ፩ ቀን የኾነው፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ፡ በእኛው፡ በመለኮታዊው የዐዋጅ ቃላችን፡ ራሷን፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ የገለጠችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን፡ ከመጀመሪያው አንሥተው፡ ይፈጽሙትና ያከብሩበት ወደነበረው ወደጥንታዊው ጥንተ ዕለቱ፡ በይፋ እንዲመለስ በማድረጓ መኾኑን እንድታውቁት ይኹን!

ይህም የኾነው፡ እንዲያው ያለበቂ ምክንያት አይደለም፤ እርሱም፡ ይህ ነው፡- የዚችው የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ የታወቁት ተጻራሪዎቿ የኾኑት፡ በይበልጥ፡ የኦሪታውያኑ አይሁድ ካህናትና የኦርቶዶክሳውያኑ ግብፆች መነኮሳት፡ ከሌሎቹ መሰሎቻቸው ወገኖች ጋር ተመሣጥረውና ተባብረው፡ በእርሷ ላይ ሲያካኺዱ በኖሩት የጥፋት ዘመቻቸው፡ ያንን፡ በመስከረም ፩ ቀን ይውል የነበረውን፥ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችንም፡ በዚያው ዕለት ያከብሩት የነበረውን፡ የእኔንና የልጇ የወዳጇን የኢየሱስ መሲሕን የልደታት ቀን፡ ከዚያ ጥንተ ዕለቱ አንሥተው፡ ወደታኅሣሥ ፳፱ ቀን ማምጣታቸው ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬም እንኳ፡ ያው የመስከረም ፩ዱን ቀንም፡ በእነርሱ፡ የዐሥር ቀኖች የጭማሪ ልዩነት እንዲኖረው ተደርጎ፡ ወደSeptember 11 (ሴፕቴምበር ኢለቨን)ንነት እንደለወጡት ታውቃላችሁ።

ልክ እንደዚያው ኹሉ፡ አኹንም እንዲሁ፡ ጥር ፩ ቀን ይውል የነበረውን፥ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችንም፡ በዚያው ዕለት ያከብሩት የነበረውን፡ የልጇ የወዳጇን የኢየሱስ መሲሕን፡ የጥምቀት ቀን፡ ይህንኑ ዐሥር ቀናቸውን በመጨመር፡ በተለመደው ድፍረታቸውና ማናለብኝነታቸው፡ ወደጥር ፲፩ ቀንነት እንዲለወጥ አድርገውት ስለነበረ ነው።

የልጇ የወዳጇ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ የትስብእታዊ ፅንሰቱ ዕለት፡ ታኅሣሥ ፩ ቀን፥ የትስብእታዊ ልደቱ ዕለት፡ መስከረም ፩ ቀን፥ የትስብእታዊ ትንሣኤው ዕለት፡ ሚያዝያ ፩ ቀን እንደመኾኑ መጠን፡ የትስብእታዊ ጥምቀቱም ዕለት፡ በጥር ፩ ቀን መኾኑ፡ እያንዳንዱ መለኮታዊ ትንግርት የሚፈጸመው፡ አንድ ዓይነት በኾነው፡ በየወራቱ መባቻ [መግቢያ] ላይ መኾኑን ያረጋግጣል።

፲፬ኛ፡ ጥር ፯ ቀን፡ እግዚአብሔር አብወእም፥ እግዚአብሔር ወልድ፥ እግዚአብሔር መንፈስ-ቅዱስ፡ በአንድ አምላክነትና በቅድስት ሥላሴነት ህልዋን ኾነን የምንኖር፥ በፍጥረታችን የምንመለክና የምንመሰገን፥ ለፍጥረታችን፡ በአባትነትና በእናትነት፥ በወንድምነትና በእኅትነት፥ በመጋቢነትና በአገልጋይነት የምንገለጥ፥ ይህንኑ ፍጥረታችንንም፡ በቸርነት ልግሥናችንና በርኅራኄ ጥበቃችን፡ አንከባክበን የምናኖር መኾናችንን የምታዘክሩበት ዕለት ስለኾነ፡ "የአስተርእዮ ቅድስት ሥላሴ በዓል" ብላችሁ፡ በመታሰቢያነት ታከብሩታላችሁ።

፲፭ኛ፡ ጥር ፲፪ ቀን፡ "የቃና ዘገሊላ ሠርግ በዓል" ተብሎ፡ በአንድ ወገኑ፡ ሥርዓተ-ጋብቻ፡ ከፍጥረተ-ዓለም በፊት፡ በመለኮታዊነቱ፥ ከፍጥረተ-ዓለም በኋላም፡ በትስብእታዊነቱ፡ በእኛ ፈጣሪነት ተሠርቶና ተፈጽሞ፡ ቅዱስና የተባረከ፥ ፍሬያማና ሕያው መኾኑ ተረጋግጦ የተመሰከረበት ነው፤

በሌላ ወገኑ ደግሞ፡ እኔ፡ ድንግል ማርያም፡ እግዚአብሔር እም የተዋሓደችኝ፡ መንበረ-ጸባዖት ቅድስት ሥላሴና ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኔ፥ ልጄ ወዳጄ ኢየሱስም፡ እግዚአብሔር ወልድና መሲሕ መኾኑ፡ ለዓለሙ ኹሉ፡ በይፋ ተገልጦ የታወቀበት መድረክና ዕለት በመኾኑ፡ በመታሰቢያነት ታከብሩታላችሁ።

፲፮ኛ፡ ጥር ፳፩ ቀን፡ እኔ፡ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም፡ በምድር ላይ፡ በሰውነት ተገልጬ፡ ከፍጥረተ-ዓለም አስቀድሞ፡ በመለኮትነት የወለድሁትን ልጄን ወዳጄን እግዚአብሔር ወልድን፡ ኋላ፡ በፍጥረተ-ዓለሙ ዘመነ-ሥጋዌ፡ "ኢየሱስ መሲሕ" በተባለበት፡ በትስብእትነት ስሙ ወልጄው፡ እኔ በመድኀኒትነቴ፡ ፍጥረተ-ዓለሙን ሳድን፥ እርሱ ደግሞ፡ በዲያብሎስ አበጋዝነት፡ ለዝንተ-ዓለም ሲካኼድ የኖረውን፡ መንፈሳዊዉንና ሥጋዊዉን ጦርነት፡ በፍቅር ተጋዳይነቱ፡ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ፡ በመስቀል ሞቱ ድል በማጠናቀቅ፡ ሰላምን፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ አጎናጽፎ፡ እርሱም፥ እኔም፡ የእናትና ልጅ ተልእኳችንን ፈጽመን፡ እርሱን፡ በዕርገቱ ካሰናበትሁ በኋላ፡ እኔም፡ በጊዜዬ፡ በሕይወተ ሥጋ እያለሁ፡ ወንዶችንም፥ ሴቶችንም ሓዋርያት አሰናብቼ፡ ወደሰማያዊቷ ገነት የተነጠቅሁባት ዕለት ስለኾነች፡ "በዓለ-ፍልሰታ፡ ዘአስተርእዮ ድንግል ማርያም" ብላችሁ፡ በመታሰቢያነት ታከብሩዋታላችሁ።

፲፯ኛ፡ ጥር ፳፰ እስከ፴ ቀን፤ እነዚህ፡ ሦስት ቀኖቿ፡ በያመቱ ይለዋወጡ የነበረችው፥ ከሰኞ እስከረቡዕ ያሉት፡ ተከታታይ ዕለታቷ ግን ሳይለዋወጡ፡ ትፈጸም የነበረችው፡ የቀድሞዋ ጾም፡ "ጾመ-ነነዌ" ትባል እንደነበረ ታስታውሳላችሁ፤

ኋላ በመካከሉ፡ ይህን፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለውን፡ የዚህን ዘመን፡ ከሃዲና ዓመፀኛ፥ አመንዝሪና ክፉ ትውልድ ሊቀጣ፡ የፍርድ ሠይፍን ታጥቆ የተላከው ደርግ፡ ከተነሣበት፡ ከሺ፱፻፷፯ ዓ. ም. ጀምሮ፡ በእናንተ በዛሬዎቹ፡ ታማኞቹ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ፡ ይህችው ጾም፡ "ጾመ-**ኢትዮጵያ"** ተብላ፡ ለአርባ ዓመታት፡ በሱባኤ ምሕላ መልክና ይዘት ስትጾም እንደቆየች ታውቃላችሁ፤

ቀጥሎ፡ ይህችው፡ የሱባኤ ጾምና የምሕላ ጸሎት፡ ከፊታችን ደርሳ፡ የኪዳነ- ምሕረት ቸርነታችንን ጸጋ ስላስገኘች፡ ደርግ፡ ተልእኮውን እንዲያበቃ አድርገን፡ ከሥልጣን እንዳስወግደነው ትመሰክሩላችሁ፤

በመጨረሻም፡ የአኹኖቹም ተተኪዎች፡ በሥልጣን መሥራት እስኪጀምሩ ድረስ፡ በርስተ-ጉልት ምድራችንና በቃል-ኪዳን ሕዝባችን ላይ፡ አንዳች ጥፋትና ዕልቂት እንዳይደርስ ያደረግነውን መለኮታዊ ጥበቃ ታዘክሩላችሁ፤

በእነዚህ ኹሉ ትንግርቶች፡ ልክ፡ **የአርባው ዓመት፡ የጾመ-ኢትዮጵያ ሱባኤ ሲፈጸም፡ የቅጣቱ መከራ ዘመን አብቅቶ፡ እነሆ፡ የምሕረቱና የምሥራቹ ጊዜ የጀመረ መኾኑን የሚያበሥረው መለኮታዊው ዐዋጃችን፡ በእኔ ቃል እንደተነገረ፡** የተገነዘባችሁት፡ የቅርብ ጊዜ እውነታ ነው።

ስለዚህ፡ እነዚህ ሦስት ዕለታት፡ በመላው ፍጥረተ-ዓለም፥ በተለይም፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያትና ኢትዮጵያውያን ልጆቼ ዘንድ፡ በየዓመቱ፡ "በዓለ-ኢትዮጵያ" ተብለው፡ እንዳለፉት ዘመናት፡ **ቋሚዎቹ የጥር ፳፰ እስከ፴ ቀኖቻቸው፡** የሚለዋወጡ ሳይኾኑ፥ ዟሪ ዕለቶቻቸው፡ ሰኞ፥ ማግሰኞና ረቡዕ ግን፡ የሚለዋወጡ ኾነው፥ ጊዜያቸውም፡ የምሕላና የጾም ሳይኾን፡ በፍጹም የዝማሬና የማኅሌት ምስጋና፥ በታላቅ ኹለንተናዊ ሓሤት፥ በፋሲካ የአለባበስ ድምቀትና የድግሥ ሥርዓትም የሚከበሩ ይኾናሉ።

በዚህ ረገድ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡ በእኔ በእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያምና በልጇ በወዳጇ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ የዐዋጅ ቃል፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ፡ በይፋ ተገልጣ፡ የዕውቀትና የእውነት፥ የቸርነትና የአገልግሎት በረከቷን፡ በቀጥታ፡ በእኛው አማካይነት፡ ለፍጡሮቿ ኹሉ ማዳረሷን ትቀጥላለች።

በአጠቃላይ፡ ከመለኮታዊዉና ትስብእታዊው ፅንሰት፥ እንዲሁም፡ አስተርእዮ [መገለጥ] እና የሰማያዊ ፍልሰት ምሥራች የተነሣ፡ በታኅሣሥ ፴ ቀን ከሚጾመው የአንዲት ዕለት ገሀድ [የጥምቀት ዋዜማ ጾም] በቀር፡ ከታኅሣሥ ፩ እስከጥር ፴ ቀን ድረስ ያሉትንና እነዚህን ተከታታይ የመታሰቢያ በዓላት ያካተቱትን፡ ዕለታት የምታከብሩዋቸው፡ ያለጾም፡ በፋሲካ የሓሤት ሥርዓት ይኾናል።

እንግዴህ፡ በገዛ ፍላጎታችሁና ምርጫችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ወደእኛ ያቀረባችሁ ልጆቻችን! ፈጽማችሁ ደስ ይበላችሁ!

በዚህ አንጻር፡ በገዛ ፍላጎታችሁና ምርጫችሁ፡ እየራሳችሁን፡ ከእኛ ያራቃችሁ ፍጡሮቻችን ደግሞ! ከዚህ የበለጠ የምናበረክትላችሁ፡ "ምን ምሥራችና ደስታ፥ ሰላምና ዕረፍት አለ!" ትላላችሁ? የለም። አዎን! ስለሌለ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ እየራሳችሁን፡ በእውነተኛ የቅጽበት ንስሓ እየመለሳችሁ፡ ወደእኛ ቅረቡ!

**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን፡**
**በባዕዳን የማሰነውን፡ የቀን አቆጣጠር ሥርዓቷን፡**
**ከ፳፻፱ [ከ፪ሺ፱] ዓመተ-ምሕረት ጀምሮ፡**
**ወደጥንተ-ኢትዮጵያዊነቱ መመለሷን እንድታውቁት ይኹን!**

"ጾመ-ነነዌ"ን መነሻ የሚያደርገው፡ የባዕዳኑ የአይሁድ አሪትና የግብፃውያኑ ኦርቶዶክስ የአጽዋማትና የበዓላት ቀመር የተመሠረተው፡ በተሳሳተ ይትበሃል ላይ በመኾኑ፡ ከዚህ ከበዓለ ኢትዮጵያ፡ የሦስት ቀናት አከባበር ጀምሮ ያለው ስሌት፡ ወደቀደመው የኢትዮጵያዊነት ሥርዓቱ እንዲመለስ አድርገናል።

ይህም የኾነው፡ አኹንም፡ እንዲያው፡ ያለበቂ ምክንያት አይደለም። በቂ ምክንያት አለ፤ ይኸውም፡ ክርስቲያኑ ዓለም፡ ልጄን ወዳጄን ኢየሱስ መሲሕን ሰቅለው በመግደላቸው፡ በአይሁድ ላይ ባለው የግብዝነት ጥላቻና ተቃውሞ የተነሣ፡ "የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የ'ስቅለት'፡ ዓርብ፥ የ'ቅዳሜ ስዑር'፡ ሰንበትና የ'ትንሣኤ'፡ እሑድ የኾኑት፡ እነዚህ ሦስት ዕለታት፡ ቀደም ብለው፡ በዚሁ፡ በክርስቲያኑ ዓለም፡ ለአይሁድ የተሰጡ በመኾናቸው፥ ከዚህ የተነሣ፡ ለአይሁድ ባለቤትነት ከተዳረጉት፡ ከእነዚህ፡ የጥንተ-ስቅለት ዓርብ፥ የጥንተ-ቅዳሜ ስዑር ሰንበትና የጥንተ-ትንሣኤ እሑድ ጋር፡ በየዓመቱ የሚመላለሱት፡ የክርስቲያኑ ዓለም፡ የስቅለት ዓርብ፥ የቅዳሜ ስዑር ሰንበትና የትንሣኤ እሑድ፡ በምንም መንገድ፡ አንድ ኾነው ተጋጥመው እንዳይከበሩ!" በሚለው፡ በክርስቲያኑ ዓለም የቀኖና ውሳኔ የተበየነ በመኾኑ ነው።

ነገር ግን፡ ይህ የቀኖና ውሳኔ፡ በእኛ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ዘንድ፥ እንዲሁም፡ በቅዱሱ ኪዳን ታማኞቻችን በኾኑት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቻችን ዘንድ፡ ተቀባይነትን ሊያገኝ ያልቻለ፡ ስሑት የጥፋት ይትበሃል ኾኖ ተወግዶ ኖርዋል፤ "ክርስቲያን ነኝ!" የሚለው ዓለም፡ ይህንኑ ስሑት ይትበሃሉን፡ በእውነተኛ ንስሓ እስካላስተካከለ ድረስ፡ አኹንም፥ ወደፊትም፡ እንደተወገደ ይቆያል። ምክንያቱም፡-

፩፤ ቀድሞውኑስ፡ ሰንበትን፡ ለእስራኤል ልጆች የሰጠ ማነው? የኢትዮጵያ፡ እግዚአብሔር መንግሥታችን ፀር የኾነው፡ መላው የክርስቲያኑ ዓለም አይደለምን? አዎን! ነው እንጂ። እንዲህ ከኾነ፡ የክፉው አበጋዝ፡ የዲያብሎስ ተከታይና አገልጋይ በመኾኑ፡ ይህን ታላቅ የክህደትና የዓመፅ፥ የአምልኮ አመንዝራነትና የጥፋት ኃጢኣት ለመፈጸም፡ ከመዳፈሩ በቀር፡ ታዲያ! ይህን ስሕተትና ጥፋት፡ ለማድረግ፡ መብቱንና ሥልጣኑን፡ ለእርሱ፡ ማን ሰጠው? ምንስ አገባው?

እንኳንስ፡ ዘሮቹ የኾኑት፡ እነርሱ፡ የእስራኤል ልጆች ይቅሩና፡ እነርሱ፡"አባታችን" የሚሉት፡ ታማኞችን አብርሃምስ እንኳ ቢኾን፡ በኢትዮጵያዊው ታማኝ ካህናችን፡ በመልከ-ጼዴቅ አማካይነት፡ አምልኮተ-እግዚአብሔርን ዐውቆና ተምሮ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፥ ለግርዛትም ቃል ኪዳን እስኪበቃ ድረስ፡ ከጣዖት አምልኮ በቀር፡ ከዚያ በፊት፡ እርሱም፡ አብርሃም፥ እነርሱም፡ ዘሮቹ የእስራኤል ልጆች አይሁድ፡ ከቶ፡ ስለእኛ ሰንበት፡ ምን የሚያውቁት ነገር ኖሮ ነው፡ "ሰንበተ-አይሁድ"፥ "የአይሁድ ሰንበት" ተብላ፡ ይህችው ሰንበታችን፡ ለእነርሱ፡ ለአይሁድ ንብረትነት የተዳረገችው? በዚህ ረገድ የተደረገው፥ እየተደረገም ያለው ኹሉ፡ የእኛ የእግዚአብሔር ሳይኾን፡ ፈጽሞ ሰይጣናዊ መኾኑ፡ ይኸው፡ በዚህ ድርጊት፡ ለማንም፡ በግልጽነት ይታያል።

ኧረ ለመኾኑ፡ ጥንቱኑ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች!"፥ ኋላም፡ "የኢትዮጵያ ልጆች!" የተባሉት፡ በእኛ ዘንድ፡ በአምልኮ ፍላጎታቸውና ምርጫቸው፥ እውነተኝነታቸውና ፍቅራቸው፥ ታማኝነታቸውና ጽናታቸው፡ ከኹሉ የዓለም የሰው ዘሮች ይልቅ፡ ቀድመውና በልጠው የተገኙት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቹ፡ ወዴት ኼዱና ነው፡ ሰንበታችን፡ ለእነዚህ፡ ለብዙ ሺህ ዓመታት፡ በአምልኮ ጣዖት ቆይተው፡ ለአምልኮተ-እግዚአብሔር ለበቁት፥ ኋላ-መጤዎች ለኾኑትና ምንጊዜም፡ ጣዖት ማምለክን ለሚወድዱት አይሁድ፡ ልትዳረግ የቻለችው?

ሰንበታችን፡ ለማንም አትሰጥም እንጂ፡ የምትሰጥ ቢኾንማ ኖሮ፡ ለዚህ ብቁ ባለመብቶቹ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቹ ኾነው፡ እናታቸው በኾንሁት፡ በእኔ፡ "ሰንበተ-ኢትዮጵያ!" ልትባል በተገባት ነበር። ለዚህ እውነታ ማረጋገጫ፡" "'<u>አኮ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ አንትሙ በኀቤየ፡ ደቂቀ እስራኤል!</u>' ይቤ እግዚአብሔር፡ ዘኵሎ ይመልክ ስሙ።

"ስሙ፡ 'ኹሉን የሚገዛ' የኾነ እግዚአብሔር፡ <u>‹እናንተ የእስራኤል ልጆች! እናንተ፡ በእኔ ዘንድ፡ እንደኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁም።›</u> አለ።" የሚለው የነቢያችን፡ የአሞጽ ቋሚ ትንቢታዊ ቃል፡ በቂ ምስክርነት ያለው ስለኾነ፡ ከቶ፡ ሌላ ማስረጃ የሚያስፈልገው አይደለም። (አሞ. ፱፥ ፯።)

፪፡ እነዚሁ ተፃራሪዎች የኾኑት የክርስቲያኑ ዓለም ወገኖች፡ የእኛ መለኮታዊ ሥራ የተፈጸመባቸውን፡ እውነተኞች ቀኖች የማናወጡ ልማዳቸውና የእኔ የኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነውን መልካም ነገር ኹሉ፡ የማጥፋቱ ዝንባሌ የተጠናወታቸው በመኾኑ እንጂ፡ ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡

-በቅድሚያ፡ የስቅለቱን መከራና የመስቀሉን የሞት ጽዋ የተቀበለባትን ጥንተ-ዕለተ-ዓርብን፥

-ቀጥሎ፡ የመጨረሻው የፋሲካ በግ ኾኖ፡ በመስቀል ላይ የታረደባት በመኾኗም፡ "ታላቅ" የተባለችውንና በመቃብር ተኝቶ ያረፈባትን፡ ይህችኛዋን የተለየች ጥንተ-ዕለተ-ሰንበት፥

-በማብቂያውም፡ ይህችኑ አንዲት ሰንበት፡ ለቀደመችው ዘለዓለማዊት ሰንበትነቷ ሊያበቃት፡ ከሙታን ተለይቶ የተነሣባትን ጥንተ-ዕለተ-እሑድ፡ በመታሰቢያነት አጽንተው መያዝና በሕያው ቅርስነት እያከበሩ መኖር በተገባቸው ነበር።

ነገር ግን፡ ይህን በማድረግ ፈንታ፡ የልጇን የወዳጇን የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ መላውን የሰውነት አካሉን፡ በደም እስኪታለል [እስኪነከር] ድረስ፡ በጭካኔ ገርፈውና በመስቀል ላይ አሠቃይተው፡ በግፍ ለገደሉት ለአይሁድ፡-

-እነዚህኑ የተቀደሱትን ሦስት ታላላቅ መለኮታውያት ዕለታት፡ እንደሽልማት፡ አሳልፈው ሰጥተው፥

-ከእውነተኛው የሥር መሠረትና ጥንታዊ የጊዜ መደባቸውም ነቃቅለውና አነሣሥተው፥

-በሌላም የሓሰትና የምትሓት ዕለታት ለውጠው በመተካት፡ እንዴት፡ የልጇ የወዳጇን የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን በዓላት፡ እንዲህ ሊያረክሱ፥ ሊያጎድፉና ሊያዋርዱ ደፈሩ?

ይህን የመሰለውን ድፍረት መፈጸማቸው፡ የቀድሞውን ሳጥናኤል፥ የኋለኛውንም፡ ዲያብሎስን ያስመሰላቸው ከመኾኑ በቀር፡ በምንም የተገባቸውና የጠቀማቸው ኾኖ አልተገኘም። በውኑ፡ "ጠላቶቻችን ናቸው!" ያሏቸውን አይሁድን ለማጥቃት ሲሉ፡ የእኛ የእግዚአብሔር የኾነውን፡ ቅዱሱንና መለኮታዊዉን ሥርዓት ማፍረስ፡ ይገባቸው ነበርን? አይገባቸውም። አግባብስ ነውን? አይደለም። እንዲያውም፡ በዚህ ክፉ ድርጊታቸው፡ እነዚህኑ፡ "ጠላቶቻችን ናቸው!" ያሏቸውን አይሁድን፡ በበለጠ ጠቀሚቸው፤ አከበሩዋቸው፤ አሠለጠኗቸው፤ አላቋቸው፤ አስቀደሚቸውም።

ስለዚህ፡ ከእነዚህ የተቀደሱና የተከበሩ መለኮታውያት ዕለታት ጋር የተያያዙትን አጽዋማትና በዓላት፡ በኢትዮጵያዊው የቀመር ሥርዓት መሠረት፡ ከዚህ አከታትዬ በምገልጻቸው፡ በእውነተኞቹ ቀኖቻቸው እየዋሉ፡ አጽዋማቱን፡ እንድትጾሚቸው፥ በዓላቱንም፡ እንድታከብሯቸው ይኹን!

፲፰ኛ፡ <u>የካቲት ፯ ቀን፤ ሰኞ፡</u> እናንተ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቼ፡ በሕዝባዊው አነጋገራችሁ፡ "ሑዳዴ" የምትሉት፡ የዓቢይ-ጾም መታሰቢያ ጾማችሁ፡ መግቢያ ይኾናል።

፲፱ኛ፡ <u>የካቲት ፲፫ ቀን፤ ሰኞ</u> ደግሞ፡ "የጌታ ጾም" የምትሉት፡ የልጇ የወዳጇ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ የአርባ ቀን መታሰቢያ ጾማችሁ፡ መግቢያ ይኾናል።

፳ኛ፡ <u>የካቲት ፲፮ ቀን፣</u> ፍጥረተ-ዓለሙን፡ ለመጨረሻውና ለዘለዓለማዊው ደኅንነትና ሰላም ያበቃው፥ ያ፡ በእኔ፡ በእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያምና በልጁ በወዳጁ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ መለኮታዊና ትስብእታዊ መሥዋዕትነትና ቤዛነት የተገኘው፡ የሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት ፍጻሜና ማኅተም የኾነው፡ የኪዳነ ምሕረት መታሰቢያ ዕለት ስለኾነ፡ "በዓለ-ኪዳነ ምሕረት" ተብሎ የሚዘከርና የሚከበር ይኾናል።

፳፩ኛ፡ <u>መጋቢት ፳፭ ቀን፣ ሰኞ፡</u> የልጁ የወዳጁ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ የሰሙነ ሕማማቱ [የመከራዎቹ ሳምንት] መታሰቢያ ሱባኤያችሁ፡ መግቢያ ይኾናል።

፳፪ኛ፡ <u>መጋቢት ፳፰ ቀን፣ ሓሙስ፡</u> ልጁ ወዳጁ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ "ወኢትረስዩ ቤተ-አቡየ፡ ቤተ-ምሥያጥ! ቤትየሰ፡ ‹ቤተ-ጸሎት› ይሰመይ! ወአንትሙሰ፡ ረሰክምዎ፡ በአተ-ፈያት፥ ወሰረቅት!

"የአባቴን ቤት፡ የገበያ መደብር አታድርጉት! ቤቴማ፡ 'የጸሎት ቤት' ይባላል እንጂ፡ እናንተ እንዳደረጋችሁት፡ የሌባ ዋሻ፥ የወንበዴ መሸሻ አይደለም!" ባለው፡ በቤተ-መቅደስ ሳይኾን፡ በአንድ ግለሰብ መኖርያ ቤት ውስጥ፡ የደቀ-መዛሙርቱን እግር በማጠብ፡ የትሕትና አገልግሎትን፥ በቅዱስ ሥጋችንና በክቡር ደማችን ያገዘፍነውን፡ የቅዱስ ቍርባንን ምሥጢር ገልጦ፥ ሥርዓቱንም መሥርቶ የፈጸመባት ዕለት ስለኾነች፡ "ምሴተ-ሓሙስ" ብላችሁ፡ በመታሰቢያነቷ ታከብሩዋታላችሁ። (ዮሐ. ፪፥ ፲፮። ማቴ. ፳፩፥ ፲፫።)

፳፫ኛ፡ <u>መጋቢት ፳፱ ቀን፣ ዓርብ፡</u> የልጁ የወዳጁ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ የስቅለቱና የመስቀለ ሞቱ መታሰቢያ ዕለት ኾኖ፡ "በዓለ ስቅለተ ሞት" ብላችሁ በማዘከር፡ ታከብሩታላችሁ።

፳፬ኛ፡ <u>መጋቢት ፴ ቀን፣ ሰንበት፡</u> ልጁ ወዳጁ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመቃብር ያረፈባት ሰንበት መታሰቢያ ዕለት ኾና፡ "ታላቂቱ ሰንበት" ብላችሁ በማዘከር፡ ታከብሩዋታላችሁ።

፳፭ኛ፡ <u>ሚያዝያ ፩ ቀን፣ እሑድ፡</u> ልጁ ወዳጁ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመንፈቀ ሌሊት፡ ከሙታን ተለይቶ የተነሣባት የዘለዓለማዊቷ ሰንበት መታሰቢያ ዕለት ኾና፡ "በዓለ-ትንሣኤ" ብላችሁ በማዘከር፡ ታከብሩዋታላችሁ።

እኒህ፡ ሦስቱ ዕለታት፡ እነርሱም፦

በቀዳሚነት፡ "በዓለ ስቅለተ ሞት" የተባለው፡ የልጇ የወዳጇ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ የስቅለቱና የመስቀለ ሞቱ፡ ጥንተ-ዕለት የኾነው፡ <u>የመጋቢት ፳፱ ቀን ዓርብ፤</u>

በተከታይነት፡ "ታላቂቱ ሰንበት" የተባለችው፡ ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመቃብር ያረፈባት ሰንበት፡ ጥንተ-ዕለት የኾነው፡ <u>የመጋቢት ፴ ቀን ሰንበት፤</u>

በማብቂያነትም፡ "በዓለ-ትንሣኤ" የተባለው፡ ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመንፈቀ ሌሊት፡ ከሙታን ተለይቶ የተነሣባት፡ ጥንተ-ዕለት የኾነው፡ <u>የሚያዝያ ፩ ቀን እሑድ፤</u>

እያንዳንዳቸው፡ በዚያው በጥንተ-ዕለታቸው፡ የዋሉ ኾነው በተገኙበት፡ በዚህ በዘንድሮው በ፳፻፱ [፪ሺ፱] ዓመተ ምሕረት፡ እነዚህኑ ሦስቱን የተለዩ ዕለታት የሚመለከተው፡ ይህ ዐዋጅ፡ በእኔ ቃል እንዲነገር ያደረግነው፡ እውነተኛውና ትክክለኛው የቀን አቆጣጠር ቀመር፡ ይህ ኢትዮጵያኛው የቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት ለመኾኑ ማረጋገጫ ምስክርነቱን እንዲያበረክትላችሁ ብለን ነውና፡ ይህን እውነታ ልታስተውሉት እንደተቻላችሁ፡ ኪዳናዊ ልጅነታችሁ፥ ክህነታችሁና ነጋሢነታችሁ አሳውቆናል።

ከዚህ በኋላና እንግዴህ ወዲህ፡ በእየዓመቱ የሚቀጥለው፡ የቀመሩ መደበኛው ሥርዓት፡ ይኸው ይኾናል። ይህም፡ "የልጇ የወዳጇ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፦ ፩. የስቅለቱና የመስቀለ ሞቱ ዕለት፡ <u>ከዓርብ፥</u>

፪. በመቃብር ያረፈባት የታላቂቱ ሰንበት ዕለት፡ ከቀጣይዋ <u>ሰንበት፥</u>

፫. ከሙታን ተለይቶ የተነሣባት የትንሣኤም ዕለት፡ ከተከታይዋ <u>እሑድ</u>፡ ከእነዚሁ ጥንተ-ዕለታት ሳይወጡ፡ እነዚሁ <u>መጋቢት ፳፱ ቀን፥ መጋቢት ፴ ቀንና ሚያዝያ ፩ ቀን፡ እነዚህ ሦስቱ፡ በሙሉ፥ ቢያንስ ቢያንስም፡ ኹለቱ የወራት ቀኖች በሚገኙበት ሳምንት ውስጥ</u> እንዲውሉ ታደርጋላችሁ!" ማለት ነው።

ይህ ሥርዓት፡ ተመርጦ ሲሠራበት የተኖረው፡ ከመደበኛ ቦታቸው ሊነዋወጡ የማይገባቸው፡ እነዚህ፡ ሦስት ሥዩማን ዕለታት፡ በየዓመቱ ዑደታቸው፡ የወሮቻቸውና የዕለቶቻቸው ቀኖች፡ በነባሩ ጥንታዊነታቸው፡ ጸንተውና ገጥመው ላይገኙ ስለሚችሉ፡ ይኸው መዛነቃቸው፡ ቢበዛ፡ ከሳምንት የጊዜ ክልል ዐልፎ እንዳይወጣ በማገድ፡ ወራቱንና ዕለታቱን እንዳይለቁ ለማድረግ ስለሚያስችል ነው። ስለዚህ፡ ሦስቱ በዓላት፡ ጥንተ-ዕለታቸው፡ ከዓርብ፥ ከሰንበትና ከእሑድ ሳይናወጽ፡ በእነዚሁ ዕለታት ይዘከሩ ዘንድ፡ እነዚሁ ሦስቱ፥ ወይም ኹለቱ የወራቱ ቀኖች በሚገኙባቸው ሳምንት ውስጥ ባሉት፡ በሦስቱ የዓርብ፥ የሰንበትና የእሑድ ዕለታት እንዲውሉ ተደርገው በእያመቱ ይከበራሉ።

፳፮ኛ፡ ግንቦት ፲ ቀን፤ ሐሙስ፡ እኔ እናቱ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም፡ በሴቶችና በወንዶች ደቀ-መዛሙርቱ መካከል በተገኘሁበት፡ ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ከሙታን ተለይቶ በተነሣ፡ በአርባ ቀኑ፡ በሰዎች ስባሔ፥ በመላእክትም ይባቤ ወደሰማይ ዙፋኑ ያረገባት፡ የዕርገቱ መታሰቢያ ዕለት ስለኾነች፡ **"በዓለ-ዕርገት"** ብላችሁ በማዘከር፡ ታከብሩዋታላችሁ።

፳፯ኛ፡ ግንቦት ፳ ቀን፤ እሑድ፡ በኦሪቱ፡ "በዓለ-ሃምሳ" ይባል የነበረው፡ ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ ባረገ፡ በዐሥረኛው ቀን፥ ከሙታን ተለይቶ በተነሣም፡ በአምሳኛው ቀን፡ እግዚአብሔር መንፈስ-ቅዱስ፡ በሓዋርያቱ ላይ የወረደበትና መላውን ዓለም የመላበት ዕለት ስለኾነ፡ **"በዓለ-መንፈስ ቅዱስ"** ብላችሁ፡ በማዘከር ታከብሩታላችሁ።

፳፰ኛ፡ ግንቦት ፳፩ ቀን፤ ሰኞ፡ **"ጾመ-ሐዋርያት"** የተባለው፡ እስከ ሓምሌ ፬ ቀን የሚዘልቀው፡ የሓዋርያት ጾም መግቢያ ስለኾነ፡ ይህን ጾም፡ በተወሰነለት የወራት ጊዜ፡ በመታሰቢያነት የምትጾሙት ይኾናል።

፳፱ኛ፡ ነሐሴ ፩ ቀን፤ ሓዋርያት፡ የእኔን፡ የእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያምን፡ የፍልሰታዬን ሰማያዊ ምሥጢር፡ ለማወቅ ሲሉ፡ ለኹለት ሳምንታት፡ ኹለት ጊዜያት፡ በትጋሃ-ሱባኤ የተጠመዱበት፡ **"ሱባኤ ፍልሰታ ለማርያም"** የተባለው፡ የጾምና የጸሎት ሰሞኖች መግቢያ ስለኾነ፡ እስከነሓሴ ፲፮ ቀን፡ በመታሰቢያነት ትጾሙታላችሁ።

፴ኛ፡ ነሐሴ ፲፫ ቀን፤ ልጄ ወዳጄ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በኢየሩሳሌም በሚገኝ፡ "ደብረ-ታቦር" በተባለው ለኻም ተራራ ላይ፡ ብሩህ ደመና በረበበበት ሰማያዊ ህላዌ ውስጥ፡ በዓለመ-ሥጋ ከሚኖሩት ሓዋርያቱ መካከል፡ ጴጥሮስ፥ ያዕቆብና ወንድሙ ዮሓንስ፥ በዓለመ-መንፈስ ከሚኖሩት ነቢያት መካከል ደግሞ፡ ሙሴና ኤልያስ፡ በአካል መጥተው፡ ከእርሱ ጋር እየተነጋገሩ የታዩበት፥ እርሱ፡ በግርማ እና በብርሃነ-መለኮቱ የተገለጠበት፥ **"ዝንቱ ውእቱ ወልድየ፡ ዘአፈቅር! ዘቦቱ ሠመርኩ! ወሎቱ ስምዕዎ!"**

**የምወድደው፥ በእርሱም፡ የምደሰተው፡ አንድ ልጄ፡ ይህ ነውና፡ እርሱን ስሙት!"** የሚል፡ የአባቱ፡ የእግዚአብሔር አብ ቃል የተደመጠበት ዕለት ስለኾነ፡ በዝማሬና በማኅሌታዊ ምስጋና ታከብሩታላችሁ። (ማቴ. ፲፯፥ ፩-፭።)

፴፩ኛ፡ <u>ነሐሴ ፲፮ ቀን፣</u> እኔ፡ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም፡ በመጀመሪያው ሱባኤ፡ ፍልሰተ-ትንሣኤዩን፡ በምድር ላይ፡ ለሐዋርያት የገለጥሁበት፥ በኹለተኛው ሱባኤ ደግሞ፡ በዚሁ ፍልሰተ-ትንሣኤዩ አማካይነት፡ እኒሁ ሐዋርያት፡ ወደሰማያት ተነጥቀው መጥተው፡ በጽርሐ-አርያም ባለው መንበረ ጸባዖትነቴ፡ የምገኝበትን ክብር ለማየት የታደሉበት የብቅዓት ማዕርጋቸው የሚዘከርበት ዕለት በመኾኑ፡ "በዓለ-ፍልሰተ-ትንሣኤሃ ለድንግል ማርያም" ብላችሁ፡ እስከነሓሴ ፴ ቀን ድረስ፡ ጾም በሌለበት የፋሲካ ሓሤት፡ በመታሰቢያነት ታከብሩታላችሁ።

፴፪ኛ፡ <u>ጳጉሜ ፩ ቀን፣</u> የዓመቱ ማካተቻ ሰሞንና የትንሿ የሱባኤ መግቢያ ስለኾነች፥ የነፍስ፥ የሥጋና የመንፈስ ኹለንተናችሁ የኾነውን፡ እየራሳችሁን፡ እስከጳጉሜ ፭ ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ፡ በእውነተኛው የንስሓ ጾም ጸሎታችሁ፡ ንጹሕና ዝግጁ አድርጋችሁ፡ አዲሱን ዘመን፡ በዚህ፡ በመልካሙ ኹለንተናዊ ብቅዓታችሁ ለመቀበል ይቻላችሁ ዘንድ፡ በምስጋና ደስ ብሏችሁ ጀምራችኋት፡ በምስጋና ደስ ብሏችሁ በመታሰቢያነቷ የምትፈጽሟት እንድትኾን አድርጉ!

እኒህን፡ እስከዚህ የተዘረዘሩትን አጽዋማት፡ የምትጾሟቸው፥ በዓላቱንም፡ የምታከብሯቸው፡ እንዴት ሊኾን እንደሚገባ፡ አገልጋይ ልጃችን ኤርምያስ፡ ቀደም ብሎ፡ በመልእክታቱና በመጻሕፍቱ ውስጥ፡ በሚበቃ ያብራራላችሁ ስለኾነ፡ እነዚያን ተመልከቷቸው!

**ተዐውደ፡ በግንቦት ፲፮ ቀን፥ ፳፻፰ ዓመተ ምሕረት ታወጀ።**

ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፣
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፣
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።

\+ + +